**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ የወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢሕአፓ ወክንድ)**

Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)

መጋቢት 19 2004 ዓም

## የኢትዮጵያን መምህራን ትግል በሙሉ ልብ እንደግፋለን

የኢትዮጵያ መመህራንን ታሪካዊ የትግል ታሪክ ጠንቅቀን እንረዳለን ። ባለፉት የወያኔ ድቅድቅ
የጨለማ ዘመን ፥የበደሉ እንፋሎት ከለበለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች፥ መምህሩ በግንባር-ቀደም
ይጠቀሳል።

እነሆ ዛሬ መምህሩ ታሪካዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ
ልናተኩርበትና ከጎኑ ልንቆም ይገባል ብሎ ኢወክንድ ያምናል ።

የመምህራኑ የሥራ ማቆም አድማ በሌላው ኅብረተስብ ካልታጀበ በቀላሉ ለበቀል ርምጃ እንደሚ
ዳረግ የታወቀ ነው ።

ስለዚህ ኢወክንድ ፥ ለኢትዮጵያ ተማሪዎች በሙሉ ፥ እንዲሁም በሀገር ውስጥም ሆነ በው
ጭ ለሚገኙ የኢወክንድ አባላትና ደጋፊዎቹ ጭምር የመምኅራኑን የአመፅ ትግል በሙሉ ልብ እን
ድትደገፉ ሀገራዊ ጥሪዎን ያስተላልፋል። የመምኅራኑን አድማ መቀላቀል
ወያኔን ለማስወገድ በሚደረገው ብሄራዊ ትግል ወሳኝነት ይኖረዋል ። በተለየ በሀገር ውስጥ የምትገ
ኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎች፥ የመምህራኑን አድማ በአስቸኳይ ለመቀላቀል ሀገራዊና ታሪካዊ ኃላፊነት
እንዳለባችሁ ጥሪያችንን እናስተጋባለን ።

በውጭ የምንገኝ የኢወክድ አመራርና አባላት ፥ በቅርቡ ለምንጠራው ወያኔን ተቃዋሚ
የመምህራን ትግል ደጋፊ የሆነ ፀረ ወያኔ ሰልፍ እንድትጠባበቁ ለሀገር ወዳድ ኃይሎች ጥሪውን
ያስተላልፋል ።

ፀረ ኢትዮጵያ የሆነው ወያኔ በታሪካችን ላይ የሚያከናውነውን ጥፋት በመቃወም በተከበሩ ሃይማ
ኖቶች፥ ምዕመናን፥ መቡስሊሙም ሆነ በክርስቲያኑ ላይ የሚፈፀመውን አረመኒያዊ
የጥፋት ርምጃ እየተከላከሉ ያሉ ወገኖቻችን መደገፍ ወቅታዊና አንገብጋቢ መሆኑን የሁሉ
ም ዜጋ ግዴታና ኃላፊነት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም።

ፀረ አማራ የሆኑት የወያኔ መሪዎች ፥ በአማራው ዜጋ ላይ የሚያካሂዱትን ያልተቋረጠ የማፈና
ቀል የናዜ ፓርቲ አረመኒያዊ ተግባር መወገዝ እንዳለበት ኢወክንድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

ኢትዮጵያዊ ዘለዓለማዊ ናት !
የወያኔን ቀብር እናፋጥነው !

Joineprpyl@gmail.com office- 202 291 5832 http://eprpyl.com/
www.facebook.com/eprpyl